በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል ሁለት

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## በሚከተሉት ነገሮች ከእኛ ሊገጥም/ልትገጥም የሚችል/የምትችል የሕይወት አጋር እንምረጥ

### *የትምህርት ደረጃ*

- ወደ ጋብቻ ከመሮጣችን በፊት ትምህርትን የተመለከቱ ጉዳዮችም ጥልቅና ጥንቃቄ የተመላት ትኩረት ይሻሉ፡፡ ስለዚህ የወደፊት የሕይወት አጋር ስንመርጥ፡-

1. *ለትምህርት ደረጃ ተገቢ ትኩረት እንስጥ*

   - የትምህርት ደረጃን አስመልክቶ በተጋቢዎቹ መካከል ተገቢ የሆነ መቀራረብ ከሌለ አለመግባባት ሊከሰት ይችላል፡፡
   - ለምሳሌ ወንዱ ከሴትዋ በትምህርት ደረጃዋ ላቅ ብሎ ካልተገኘ ከእርስዋ ያነሰ ሆኖ ሊሰማው ወይም ሴቲቱም ልትንቀው ትችላለች፡፡
   - ሴቲቱም በትምህርት ደረጃዋ ከወንዱ ያነሰች ሆና ባትገኝ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም በእያንዳንዱ ጉዳይ የተመጣጠነ ግንዛቤ ሳይኖራቸው ሊገኙ ወይም በጋራ አመለካከት ሊራራቁ ይችላሉና፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## *2. የትምህርት ዓይነቱም ትኩረት አይነፈገው*

- የተማርነው የትምህርት ዓይነትም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚኖረን ምልከታ ላይ ተጽእኖ የማሳደር አቅም አለው፡፡
- ለምሳሌ በሳይንሳዊ ጉዳዮች ላይ አትኩሮት በማድረግ የተማሩ ብዙ ጊዜ ነገሮችን ተንትነው የሚመለከቱና ሐሳባቸውንም በአግባብም በተደራጀ መልኩ ማቅረብ የሚያስችል አቅም ያላቸው ሆነው ሲገኙ ወደ ሰብአዊነት ያዘነበሉ ደግሞ በአስተሳሰባቸውና በጠባያቸው ትኩረት ሰጪና ተንከባካቢ ይሆናሉ፡፡
- ስለዚህ የሕይወት አጋራችን በሕይወት በተማሩት ትምህርት ሊገጣጠም የሚችለውን ሁኔታ ከተማሩት ወይም ከቀሰሙት ትምህርት አንጻር መመርመር ያስፈልጋል፡፡
- በግልና በሕዝብ ወይም በአዳሪ ት/ቤት፣ በከተማና በገጠር የተማሩም እንዲሁ ይለያያሉ፡፡ በአዳሪ ት/ቤት የኖሩ እርስ በርስ ተቀላቅሎ የመኖር ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡
- በታላላቅ ከተሞች ውስጥ ከበርካታ ነገሮች ነገሮች ጋር በመተዋወቅ የኖሩ ሰዎችና በተወሰነች ጠባብ ከተማ የኖሩ ሰዎች ስለ ሕይወት በሚኖራቸው አስተሳሰብ ስለሚለያዩ ወደ ጋብቻም ሲገቡ ይኸው ችግር በትዳሩ ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል እነዚህ ጉዳዮች በአግባብ መጤን ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ስለዚህ እነዚህ ጉዳዮች ምንም ያህል አስፈላጊ መስለው ባይታዩንም እንኳ የሕይወት አጋራችንን ስንመርጥ ግን እነዚህን ጉዳዮች መዘንጋት እንደሌለብን እናስታውሳለን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## *ማኅበራዊ ሕይወት*

- **አንዳንድ ወጣቶች ለራሳቸው ማኅበራዊ ሕይወት ትኩረት ነፍገው በማኅበራዊ ሕይወታቸው ከፍ ካለው ደረጃ ያሉትን የሕይወት አጋሮች ሊመርጡ ይችላሉ፡፡**
- **በትዳራቸው ደስታን ለሚሹ ሁሉ ግን የሚከተሉትን እንመክራለን፡-**

1. ***በማኅበራዊ ሕይወትና በኑሮ ሁኔታ ከእኛ ጋር ተመሳሳይ አቋም ያላቸውን ትኩረት እንስጣቸው***

- **ከ‹‹ስም›› ብቻ ጋር መዛመድ ደስታን አይገዛልንም፡፡**
- **ከሕይወት አጋራችን ጋር በማኅበራዊ ሕይወታችን መጣጣም ከሌለ አስቀድመው በሚመሩት ሕይወት ሲያገኙት የነበረውን ልናጎድልባቸው እንችላለን፡፡**
- **ይህም ጉዳይ ንጉሥ ሳኦል ልጁን ያገባት ዘንድ ነቢዩ ዳዊትን** ‹‹ ሳኦልም ዳዊትን፡- ታላቂቱ ልጄ ሜሮብ እነኋት እርስዋን እድርልሃለሁ ብቻ ቀልጣፋ ልጅ ሁንልኝ፥ ስለ እግዚአብሔርም ጦርነት ተጋደል፡፡» ***ቀዳ ሳሙ 18፡17፡፡*** ብሎ **በጠየቀበት ጊዜ በግልጽ ተብራርቶ ይገኛል፡፡**
- **ዳዊትም በሳኦል ጥያቄ ከመደሰት ይልቅ** ‹‹ ለንጉሥ አማች እሆን ዘንድ እኔ ማን ነኝ? ሰውነቴስ ምንድር ናት? የአባቴስ ወገን በእስራኤል ዘንድ ምንድር ነው? » ብሎ መልሶለታል፡፡ ***ቀዳ ሳሙ 18፡18፡፡***
- **የዳዊት ምላሽ ከልብ የተሰጠ ሲሆን ይህንኑ ለሳኦል አገልጋይ መልሶለታል፡፡** ‹‹ የሳኦልም ባሪያዎች ይህን ቃል በዳዊት ጆሮ ተናገሩ ዳዊትም፡- እኔ ድሀ የተጠቃሁም ሰው ስሆን ለንጉሥ አማች እሆን ዘንድ ለእናንተ ትንሽ ነገር ይመስላችኋልን? አለ። ***ቀዳ ሳሙ 18፡23፡፡***
- **ስለዚህ በትምህርትም ሆነ በማኅበራዊ ሕይወት የሚመጥነንን የሕይወት አጋር እንምረጥ፡፡**

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

2. ***ማኅበራዊ ሕይወት ቁሳዊ ነገርን ብቻ የሚዳስስ ብቻ ሳይሆን የኑሮ ሁኔታንም የሚመለከት ነው***

- ለምሳሌ በገጠርና በከተማ የሚኖሩ ባለጠጎች የአኗኗር ሁኔታቸው የተለያየ ነው፡፡ በግብርና የሚኖሩት ከነጋዴዎች ነጋዴዎቹም ከምሁራኑ ይለያያሉ፡፡
- አንድ በግብርና የሚተዳደር ሰው በንግድና ቱሪዝም የተሰማራችን የከተማዋን ሴት ቢያገባ የሚሆነውን እስኪ እናስብ!
- በማንነታችን የሚያስፈልገው መመዘኛ ሁሉ ማኅበራዊ ሕይወትንም በተመለከተ እንዲሁ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ የሕይወት አጋራችንን በምንመርጥበት ጊዜ ለተወሰኑ ጉዳዮች ብቻ አትኩሮት በመስጠት ላይ አንወሰን፡፡ በሁሉም ዘርፍ መመልከት ያለብንን እንደ አቅማችን እንመልከት፣ የእግዚአብሔርም ፈቃድ ይሆንልን ዘንድ ተግተን እንጸልይ፣ እንዲሁም የንስሐ አባቶቻችንና በዚሁ የሕይወት አቅጣጫ በቂ ልምድ ያላቸውን እንጠይቅ፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

2. <u>ልዩ ትኩረቶች በውጪ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን</u>

- ሁለት ዓይነት በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አሉ፡-

1. **በሕጋዊ መንገድ ወጥተው ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ አግኝተው የሚኖሩ፡-** ተረጋግተው ስለሚኖሩ የሕይወት አጋራቸውን ለመምረጥ የተሻለ እድል ስላላቸው ሳይጣደፉ የሕይወት አጋራቸውን መምረጥ ይችላሉ፡፡
2. **ለትምህርት፣ ለሥራ ወይም ለጉብኝት ሄደው በዚያው መቆየት ያስቻላቸው ዘንድ የሚሹ፡-** በዚያው አገር የሚያስቀራቸው/የምታስቀራቸው ‹‹የሕይወት አጋር›› ለማግኘት እጅግ ይጣደፋሉ፡፡

- በስደት አገር ጋብቻ ከሚከተሉት ሦስቱ በአንዱ ይፈጸማል፡፡

   1. *<u>የውጪ (ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ) ዜጎችን ማግባት</u>*

   - ይህም ለግል ጥቅም (የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት) ሲባል ይፈጸማል፡፡ እነዚህ ሰዎች በምድራዊው ብቻ ሳይሆን በሰማያዊ ሕይወታቸው ላይ ሳይቀር ታላቅ ስህተት ይሠራሉ፡፡
   - የትኛዋ ዘመናዊ የምዕራብ ዓለም ሴት መላ ዘመኑን በሦስተኛው ዓለም የኖረን ወንድ ለማግባት ትሻለች? መላ ዘመንዋን በኃጢአት ያጠፋች የምዕራብ ዓለም ሴት ወጣቱን ወንድ ልታገባው ልትሻ ትችላለች፡፡
   - ታዲያ ይህን የጥፋታችን ምክንያት የሆነ ‹‹እድል›› ራሴን ልጠቅምበት እችላለሁ ብለን እንቀበለዋለን? በማርጀትዋም የተነሳ ዘር ላትተካልህ ትችላለች ስለዚህም ‹‹ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፡፡›› *<u>መዝ 126(127)፡3፡፡</u>* የተባለው አይደረግልህም፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

- ራስን ለመጥቀም ተብሎ የሚፈጸምጋብቻ ከሚከተሉት ሦስት መንገዶች በአንዱ ደደፈጸማል፡፡

1. *የወረቀት ጋብቻ*

- ይህን ዓይነት ››ጋብቻ›› በጠበቃ አማካይነት ሊፈጸም ይችላል፡፡ ጠበቃውም ለዚሁ አገልግሎቱ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል፡፡
- ይህ ‹‹ጋብቻ››ም ለሁለቱ እንደሚመች ሆኖ ስለሚመራ በትዳር ሕይወት ውስጥ የሚገኘው በጎ ሕይወት አይነበብበትም፡፡ ይህም ዓይነት አካሄድ የ‹‹ክርስቲያኖች››ን በመንግሥታት ፊት አለመታመንና ወንጀል ለመፈጸም መደፋፈርን የሚያመለክት ነው፡፡
- እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች እንዲህ ያለውን የወንጀል ድርጊት በመረዳት ዜግነት የሌላቸውን የሚያገቡ ዜጎቻቸውን አስመልክቶ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጠዋል፡፡ አንደኛው ተጋቢዎቹ ከጋብቻ በፊት ቢያንስ ለሁለት ዓመት አብረው እንዲኖሩ የሚያስገድድ ሲሆን ሁለተኛው ባልና ሚስቱ ከጋብቻም በኂላ አብረው እንዲኖሩ የሚያስገድድ ነው፡፡
- ይህንም ጉዳይ ለመከታተል መንግሥታቱ በየጊዜው በየቦታዎቹ እየተገኙ ተጋቢዎቹ አብረው የሚኖሩ መሆናቸውን የሚከታተሉ ወኪሎቻቸውን ይልካሉ፡፡

2. *በየቦታው የሚፈጸም ጋብቻ*

- ይህም በቤተ ክርስቲያን ሳይሆን በየቢሮዎቹ ይፈጸማል፡፡
- ይህም የሚደረግበት ምክንያቱ የመኖሪያውን ፈቃድ ካገኙ በኂላ ፈትተው የሚፈልጉትን እንደምርጫቸው ለማግባት ስለሚያስችላቸው ነው፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

2. *በየቦታው የሚፈጸም ጋብቻ…*

- ይሁን እንጂ የመኖሪያ ፈቃዱን ለማግኘት በሚሞክሩበት ጊዜ እነዚህ ሰዎች ቅዱስ ቁርባን ባለመቀበል፣ መንፈሳዊነታቸውን በማጣት እንዴት በማመንዘር ይኖራሉ?
- ለበርካታ ዘመናት በማታለልስ መኖር እንዴት ይቻላቸዋል? እነዚህ ‹‹ባሎችስ›› የመኖሪያ ፈቃዳቸውን ካገኙ በኋላ ያገቧትን ገፍተው ሌላይቱን ለመፈለግ መሄድ እንዴት ይቻላቸዋል? ይህችስ ሴት ስለ ኢትዮጵያውያን ወንዶች የሚኖራት መጥፎ አመለካከት እንዴት የመረረ ይሆን?
- በማያውቀው የእንግድነት አገር የሚኖርስ ሰው ኑሮውን እንዴት በማታለል ይጀምራል? ይህንስ እያደረግን እያንዳንዱን አዲስ ቀን በአዲስ መንፈስ ለመቀበል በየማለዳው የምንጸልየውስ ጸሎት ትርጉሙ ምንድርነው?

3. *የቤተ ክርስቲያን ጋብቻ*

- እግዚአብሔርን በመፍራት የሚኖር ሰው ጋብቻውን በቤተ ክርስቲያን ለመፈጸም ሊወስን ይችላል፡፡ እጮኛውም ለእግዚአብሔር ስላላት ፍቅር ወይም ለቤተ ክርስቲያንም ስለመታዘዝዋ ሳይሆን ለማግባት ብቻ በመፈለግዋ የተነሳ ልትስማማ ትችላለች፡፡ ይህን በመሰለ የጋብቻ ሕይወት በርካታ ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡

*መሻትን ወይም ስሜትን ተከትሎ መሮጥ*

- ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ በርካታ በጎነት ያላቸው የውጪ ዜጎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አይጠረጠርም፡፡
- ይሁን እንጂ በርካታዎቹ በባሕል፣ በአመለካከትና በእምነት ልዩነት በሚኖሩ ክፍተቶች የተነሳ ለቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች የሚመጥኑ አይደሉም፡፡

# <u>ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ</u>

### 3. *<u>የቤተ ክርስቲያን ጋብቻ</u>*

*<u>የኢትዮጵያ ልጃገረዶችን የሚያገቡ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወንዶች</u>*

- በውጪ ዓለም የሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወንዶች ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ ሴቶችን በማግባት ከሚገጥማቸው ችግር ለማምለጥ ሲሉ ወደ አገራቸው በመምጣት የሀገራቸውን ልጃገረዶች ያገባሉ፡፡
- እነዚህም ይህን በማድረጋቸው በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ ሊገጥሟቸው የሚችሉ ችግሮችን አስተውለው አይመለከቷቸውም፡፡

*<u>እጮኛን በመምረጥ የሚኖር ችኩልነትን</u>*

- በጊዜ እጥረት የተነሳ እጮኛን በችኮላ የመምረጥ አጋጣሚ የሚፈጠር ሲሆን ይህም ምርጫ ብዙ ጊዜ የተሳሳተ ሆኖ ይገኛል፡፡
- በጊዜ ማጠር የተነሳ ያልታዩ በርካታ አለመግባባቶች ያላቸው ክፍተቶች በቀላሉ ታልፈው ሊጠገን የማይችል ስብራት ያስከትላሉ፡፡
- እነዚህ ሰዎች የጊዜ እጥረት ስለሚኖርባቸው አንዳንድ ጊዜ እጮኛ የመምረጥ እድሉን ለዘመዶቻቸው ይሰጣሉ፡፡ የሚበሉትንና የሚለብሱትን አስመልክቶ የሌሎች ሰዎችን አስተያየት ለመቀበል የማይፈቅዱ ሰዎች የተከተሉት ይህ አቅጣጫ እንደ እንግዳ ነገር የሚቆጠር ነው፡፡

*<u>ለጋብቻ መቸኮል</u>*

- ችኮላው በእጮኛ ምርጫ ብቻ ሳይሆን ጋብቻውንም ቸኩሎ በመፈጸም የሚታይ ነው፡፡
- እጮኛሞቹ እርስ በርስ ስሜታቸውንና ሐሳባቸውን ለመካፈልና ለመተዋወቅ እድል አይሰጡም፡፡

*ለጋብቻ መቸኮል*

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

- አንዳንድ ጊዜ የሚያስገርመው በጾም ወራት ከውጪ የሚመጡ እነዚህ ወንዶች እንደ ቤተክርስቲያን ትምህርትና ሥርዓት አዲሱን ሕይወታቸውን ከመጀመር ይልቅ የጊዜ እጥረቱ… ከግምት ውስት ገብቶ ጋብቻቸው በጾም ወራት እንዲፈጸምላቸው ሲጠይቁ መገኘታቸው ነው፡፡
- በችኮላ ከተፈጸመው ከዚህ ጋብቻም ቀጣዮቹ ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ፡-
  1. ባል ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ካለው ወደ መጣበት የውጪ ዓለም ሚስቱን ይዞ ይሄዳል ወይም
  2. ግሪን ካርድ ብቻ ካለው ሌሎቹን ጉዳዮች ለመፈጸም ሚስቱን ኢትዮጵያ ትቶ ለምሳሌ ወደ አሜሪካ ይመለሳል፡፡ በዚህም ሂደት የማታውቀውን ሰው በፍጥነት ያገባችው ሴት ቢያንስ ለሁለት ዓመት ጊዜ ከባልዋ ተለይታ ትኖራለች፡፡
- ከላይ ከተገለጹት ከሁለቱ የትኛውም ይፈጸም ሴቲቱ ግን ወላጆችዋንና ቤተቦችዋን እንዲሁም በአገርዋ ሳለች የለመደቻቸውን ነገሮች ሁሉ ትታ በአዲስ ማኅበረሰብና ባሕል መካከል ከማታውቀው እንግዳ ሰው ጋር አብራ ለመኖር የመሄድዋ እውነታ ግን የማይካድ ነው፡፡
- ባልም ከችኮላው የተነሳ ሚስቲቱ የማትመጥነውና የማትስማማው ሆኖ ሊሰማው ይችላል፡፡
- ሚስትም አዲሱ ማኅበረሰብ በሚከተሉት ምክንያቶች የተመሳ እንግዳ ሊሆንባት ይችላል፡-
  - ኑሮው እንደ ኢትዮጵያ ባለመሆኑና ፍጥነት ስላለበት
  - ማኅበራዊ ሕይወቱ እንደ አገር ቤት ጠንካራና ምቹ ባለመሆኑ የተነሳ ጎረቤትዋን የማወቅ እድል እንኳ ልታጣ ስለምትችል
  - ለቋንቋው እንግዳ በመሆንዋ ወይም እንግሊዝኛውም በአገር ቤት ከተለመደው ፈጠን በማለቱ
  - በሥራ ሰዓቱ ርዝመት የተነሳ ባል ደክሞ መጥቶ ተገቢ ክብካቤ ሊያደርግና ጊዜ ሊሰጥ ባለመቻሉ ቀኑን ሙሉ ብቻዋን የዋለች ሚስት በድካሙ የተነሳ ተገቢውን አያደርግላትም፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

*ውጤቱስ ምንድር ነው?*

- ***የሥነ ልቦና ችግርና የነርቮች መጎዳት***
  - *ሚስቲቱ ይህ ችግር ሊገጥማት መቻሉ የማይካድ ነው። ምክንያቱም በሥራ፣ በማኅበራዊ ሕይወት እንዲሁም ወደ ቤተ ክርስቲያንም በመገስገስ ፋታ ያልነበራት ሴት ከባልዋ ጋር እንኳ የማታወራበት ባእድ አገር ስትገኝ ምንም በዙሪያው ድሎትና ምቾት የሚገኝ ቢሆንም ትጎዳለች፤ ቀጥሎም ችግሩ ወደ ባልየው በመተላለፍ ሌሎች በርካታ ችግሮች ይፈጥራል።*
- ***ናፍቆት***
  - *በብቸንነትዋ የተነሳ ወላጆችዋንና ዘመዶችዋን ትናፍቃለች በዚህም የተነሳ ደጋግማ ስልክ መደወል ትፈልጋለች።*
  - *ይህም ሁለት ችግሮችን ያስከትላል። አንደኛው ስልክ በመደወል የተነሳ የሚከሰት ከፍተኛ ወጪ ሲሆን ሁለተኛው ወላጆችዋ ደጋግመው እንዲጎበኝዋት መፈለግዋ ናቸው። ይህም በባልየው ላይ ከፍተኛ የገንዘብ ጫና የሚፈጥር ሲሆን ትዳሩንም የሚፈትን ችግር ያስከትላል።*
- ***ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ከወላጆችዋ ጋር ለመቆየት መፈለግ***
  - *በዚህ ጊዜ ያለ ባልዋ ፈቃድ ሚስት ወላጆችዋን ለማግኘት ወደ ኢትዮጵያ ትመጣለች የቆይታ ጊዜዋንም ታራዝማለች።*
  - *ከሁሉ አስከፊ የሚሆነው ወደ ባልዋ ላለመመለስ ወስና በአገርዋ ለመቆየት መወሰንዋ ነው።*

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***ውጤቱስ ምንድር ነው?...***

- ***ለመሥራት መፈለግ***
    - ሚስት በመማረርዋ ወይም ባልዋ የገንዘብ አቅማቸውን ለማዳበር ፈልጎ ከሚያሳድርባት ግፊት የተነሳ ሥራ ለመፈለግ ልትወስን ትችላለች፡፡ ይህም ግን ወደ በርካታ ችግሮች ያመራል፡፡
        - ረጅም ሰዓት በድካም ስለምትሠራ ቤትዋን ልትተው የቤተሰብዋንም ፍላጎት ወደ መዘንጋት ያደርሳታል፡፡ ይህም የሕይወት ጫናና ንዴት ሊያበዛባት ይችላል፡፡
        - ከጊዜ ማነስ የተነሳ ልጆችዋን በልጆች መጠበቂያ ሥፍራ ለሞግዚቶች ትተዋለች፡፡ ሕጻናቱስ ከሞግዚቶቻቸው የሚማሩት ሞራልና መንፈሳዊነት ምንድር ነው? ለበጎ ነገር ተቃራኒ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል ልጆቹም ይህን በቀላሉ ይወርሳሉ፡፡ ሕጻናቱም ከወላጅ የሚገባውን ክብካቤ ስላላገኙ የሞግዚቶቻቸውን ጠባይ እየወረሱ ቀስ በቀስ ከወላጆቻቸው ራሳቸውን ያገላሉ፡፡
        - በሥራ ቦታዋም በጎ ባልሆኑ መንገዶች ተጽእኖ የሚያሳድሩባት ሰዎችን በመተዋወቅ በቂ ልምድ ከማጣትዋ የተነሳ ፈጽመው ሊያጠፏት ይችላሉ፡፡ እርስዋም ከውጪ በተማረችው እንግዳ ነገር የተነሳ በቤትዋ ያለ ግኑኝነት ይበላሻል፡፡ በመቀጠልም ከኃላፊነትዋ/ግዴታዋ ይልቅ ስለመብትዋ የምትከራከር ትሆናለች፡፡
        - *ስለዚህ ወደ ውጪ አገር ለመኖር የሚሄዱ ሚስቶች ለባሎቻችሁ ተገቢው ቅርበት እስኪኖር፣ ልጆቻችሁን እስኪያሳድጉ፣ አስቀድሞ ከሙሉ ሰዓት ሥራ ይልቅ በትርፍ ሰዓት ሥራ በመሞከር፣ ከመልካም ሰዎች ጋር የሚሆናቸውን ሥራ እስኪያገኙና እስኪያረጋግጡ ድረስ ሥራ ለመጀመር ባይቸኩሉ መልካም ነው፡፡*

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

*3. የቤተ ክርስቲያን ጋብቻ...*

*በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ልጃገረዶችን የሚያገቡ ውጪ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ወንዶች*

- የውጪውን ዓለም ለመጎብኘት ሲወጡ በዚያው ቀርተው ዜግነት ባለማግኘታቸው ካለባቸው ችግር የተነሳ በዚያው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (ኦርቶዶክሳውያን) ለማግባት የሚወስኑ ወንዶች አሉ።
- ይህ አማራጭ ትክክል ቢሆንም ከዚህ ጋብቻ ጋር የሚኖሩ ተዛማጅ ችግሮች አሉ። እነዚህም፡-

*በእጮኛሞቹ መካከል የሚኖር አለመመጣጠን*

- ሴቲቱ በምዕራቡ ዓለም የተወለደችና ያደገች ሆና ባል በኢትዮጵጳጳ ካለው የጥንቱ ባሕል ጋር ያደገ ከሆነ ሊከሰት የሚችል ችግር
- ሚስቱ በወላጆችዋ ተከባ ሲያያት ባልየው ሊሰማው የሚችለው የእንግድነት ስሜት
- ሚስቲቱ ከፍ ያለ የገንዘብ አቅም ያላት ሆና መገኘት አዲስ መጪ የሆነውን ባል የበታችነት ፣ እንግድነትና ንዴት እንዲሰማው ለማድረግ መቻሉ።

*ኑሮውን ለማመቻቸት የመሠረተው ጋብቻ ሆኖ ሊቆጠር መቻሉ*

- ሚስቲቱ ባልዋ እርስዋ የሆነችውን ተቀብሎ በመውደድ ያገባት መሆኑን ከማመን ይልቅ የመኖሪያ ፈቃዱን ለማመቻቸ ያገባት ሆኖ ሊሰማት ይችላል።
- በዚህም የተነሳ ሚስት ከባልዋ ጋር ባላት ኑሮ መረጋጋትንና ዋስትናን ታጣለች።
- ይህም ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ያልጠበቀችው ሰዓት ትቶአት ሊጠፋ እንደሚችል ታስባለች።

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## ወደ ውጪው ዓለም ለሚጓዙ ወጣቶቻችን የሚሆን ምክር

### *ለጋብቻ አትቸኩሉ*

- ከጋብቻ በፊት በምትሄዱበት አገር የሚኖራችሁ ቆይታ/ኑሮ ሕጋዊ እንዲሆን የሚያስተማምን ሥራ ልታገኙ ለምትችሉባቸው ጤናማ መንገዶች ቅድሚያ ስጡ።
- ጋብቻን ዜግነት የምታገኙበት ብልሃት አድርጋችሁ ከመቁጠር ይልቅ ሰማያዊ ዜግነት የምታገኙበት ምክንያት አድርጋችሁ ተጠቀሙበት።
- ስለዚህ የወረቀቱንም፣ የቢሮውንም፣ ኦርቶዶክሳውያን/ኢትዮጵያውያን ካልሆኑት ሁሉ ጋር የምናደርገውን ያልተጠና ጋብቻ እንተው።

### *የእጮኝነት ምርጫው የጋራ እንደሆነ እንመን*

- እጮኛችንን ራሳችን እንምረጥ።
- እጮኛን የማይመለከተው ሌላ ሰው እንዲመርጥልን አንፍቀድለት።
- በማንነታችንም ሆነ በአመለካከታችን ለእኛ የምትመጥን/የሚመጥነንን እጮኛ ለራሳችን እንምረጥ።

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***ውጤታማ የሆነ ጋብቻ/ትዳር***

**ወደውጪው ዓለም ለኑሮ የምትጓዙ ወጣቶቻችን…**

- ጋብቻችሁን በዚያው አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን/ኦርቶዶክሳውያን ጋር አድርጉ፡፡
- ምክንያቱም የአገራችንንና/የውጪውን መልካሙን ባሕል አጣምረው ስለሚይዙ፣ እጮኛን ለመምረጥ በቂ ጊዜ ስለምታገኙና እርስ በርስ ለመተዋወቅና ለመቀራረብ በቂ ጊዜ ስለሚኖራችሁ ነው፡፡
- በኢትዮጵያ ከሚኖሩት ለመምረጥ ካሰባችሁ አስቀድማችሁ በት/ቤት፣ በአንድ መንደር በመኖር… ለምታውቋቸው ቅድሚያ ስጡ፡፡ ወደ አገር ቤት መጥታችሁም ስትመርጡ በቂ ጊዜ ስጡ፣ ከጋብቻውም በፊት አብራችሁ ረዘም ያለ ቆይታ ይኑራችሁ፡፡
- ሚስትም ወደምንኖርበት አገር ስትመጣ ለቤተ ክርስቲያን በሚቀርብ ሥፍራ መኖሪያችንን እናድርግ፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች መኖሪያቸውን ወደ ሥራ ቦታቸው መቅረቡን ብቻ ያስባሉ እንጂ ወደ ቤ/ክ መቅረቡን አያስቡም፡፡
- ቤታችን ወደ ቤ/ክ መቅረቡ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እርካታ ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ከጠላታችን ዲያቢሎስ ሥራ መጠበቅን ስለምናገኝም ጭምር ነው፡፡
- ጌታችን ‹‹እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፡›› *ዮሐ 14፡6፡፡* ስላለን ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የሚያስገባን በር እንደሆነም ‹‹ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ፡፡ … እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ፡፡ ›› *ዮሐ 10፡7፣ 10፡10፡፡* ስላለን በምንኖርበት ሁሉ ወደ ርሱ በር/ደጅ ቀርበን መኖር ይገባል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

- **በውጪው ዓለም የምንጀምረውን አዲስ ሕይወት በሚጠብቀንና በሚባርከን በእግዚአብሔር እንጀምር፡፡** ‹‹ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።›› ***ዘፍጥ 12፡3፡፡***
- **ዮሴፍን በስደት አገር በግብጽ እንደባረከው ይባርከን ዘንድ በውጪው ዓለም የምንጀምረውን አዲስ ሕይወት በሚጠብቀንና በሚባርከን በእግዚአብሔር እንጀምር፡፡** ‹‹ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፥ ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነ በግብፃዊው ጌታውም ቤት ነበረ።» ***ዘፍጥ 39፡2፡፡***
- **በትዳርም ሆነ በማንኛውም ሕይወት ውጤታማ የሚያደርገን ወደእግዚአብሔር ቀርበን መኖራችን ነው፡፡**
- **አንድ በአሜሪካ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ምሁር ነበር፡፡ ይህም ሰው የሚሰራበት ታላቅ መሥሪያ ቤት ነበር፡፡ ሥራውም ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ከማስቀደስ፣ ከመማር… የሚገድቡት ብዙ እንቅፋቶች ይፈጥርበት ስለነበር መልቀቂያ አስገብቶ ሲለቅ ብዙዎች በውሳኔው ተገረሙ፡፡ እርሱም ይህን ያደረገው ስለመንፈሳዊ ሕይወቱና ቤተሰቦቹ ዘላለማዊ ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ ስላሰበ ነው፡፡**
- **ብዙም ሳይቆይ በዚያው በሚኖርበት አካባቢ ያለ መሥሪያ ቤት በጥሩ ደመወዝና በቀድሞው መሥሪያ ቤት ሳያገኝ የቆየውን ጥቅማጥቅም ጨምሮ ቀጠረው፡፡**
- **ይህን የሚበልጠውን ስጦታ ያዘጋጀለትም እግዚአብሔር ነበር፣ ከሥራው ይልቅ እግዚአብሔርን መርጧልና፡፡**
- **ስለዚህ ወገኖቼ ‹‹ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡››** ***ማቴ 6፡33፡፡*** እንዳለን አስቀድመን እግዚአብሔርን እንጂ ሥራውን አንፈልግ፡፡
- **ለቤተሰባችን ደህንነትና ዋስትና ጠንክረን በቤታችን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖርልን እናድርግ፡፡**

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org

ይቆየን።